የሰ/መ/ቁ. 23744

ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሒም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** አቶ በቀለ በድዬ

**መልስ ሰጪ፡-** 1ኛ/ የወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ

2ኛ/ የቡሌ ሆራ ከተማ አስተዳደር

3ኛ/ አቶ ሁሴን ወልዴ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ ክስ ለማቅረብ እንዲፈቀድ ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተመለከተውን ድንጋጌ አተረጓጎም የሚመለከት ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ዳኝነት ሳይከፍልበት በነፃ ክስ ለማቅረብ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ መክፈሉ በተረጋገጠ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት አለው በማለት አሰናብቶታል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

የጠ/ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ መሠረት በዳኝነት ክፍያ ክርክር ላይ ይግባኝ ሊቀርብ እንደማይችል ስለሚደነግግ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ያለውን ትዕዛዝ መስጠት በመሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከተሰጠ እንጂ በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ መጠየቅ የሚቻል ባለመሆኑ የይግባኝ አቤቱታው የሕግ አካሄድን ጠብቆ የቀረበ አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/3/ የተመለከተው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማና አስፈላጊነት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡

አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሙሉ የክርክር አካሄድን ተከትሎ የመጨረሻ ውሣኔ ለመስጠት በእያንዳንዱ የክርክር ደረጃ የሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ብይኖች ይኖራሉ፡፡ በዚህ አኳኋን በክርክር ሂደት መካከል ትዕዛዞችና ብይኖች በመስጠት ይግባኝ እንዲቀርብ ቢፈቀድ በአንድ ጉዳይ ምክንያት በተለያየ ፍ/ቤት የተለያየ ክርክር እንዲኖር የሚጋብዝ አሠራር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ክርክርን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ መቋጨት ይገባል ለሚለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ገዥ ዓላማ ጋር የሚፃረር ነው፡፡

ለዚህም ነው ማናቸውም ፍ/ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ጊዜአዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ሲሰጥ ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ለማለት አይቻልም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተደነገገው፡፡

ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች የትኞቹ ናቸው? የሚለውን ለማመልከት ከተዘረዘሩት የትዕዛዝ ዓይነቶች ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ የሚቀርብ ጥያቄ አንዱ የትዕዛዝ ዓይነት እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡

ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በቀረበ ጥያቄ ላይ ሊሰጥ የሚችለው ትዕዛዝ እንደነገሩ ሁኔታ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው ከሣሽ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችለው የገንዘብ አቅም የሌለው ስለሆነ እንደ ጥያቄው የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍል በነፃ ፋይል ከፍቶ ክሱን ለማቅረብ ይችላል የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከሣሹ ድሃ ያለመሆኑ ስለተረጋገጠ ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ካልከፈለ በቀር በነፃ ፋይል ከፍቶ ክሱን ለማቅረብ አይችልም የሚለው ነው፡፡

በመጀመሪያው አኳኋን ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት ፋይሉ ተከፍቶ ክርክሩ የሚቀጥል ነው፡፡ የክርክሩ ውጤት የሚታወቀው ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር ማስረጃ መሠረት ነው፡፡ በመጨረሻው የክርክር ውጤት ተከሣሹ ባይስማማ ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ክሱ ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ እንዲከፈት መደረጉ የሕግ ድጋፍ አልነበረውም የሚለውን እንደ አንድ የይግባኝ ምክንያት በማድረግ በውሣኔው ላይ ካለው ቅሬታ ጋር አዳምሮ ማቅረብ ይኖርበታል እንጂ ከሥረ-ነገሩ ፍርድ በፊት የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት አይኖረውም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተመለከተው ድንጋጌም በዚህ አኳኋን በሚቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ ክልከላ ለማድረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል ድሀ ያለመሆንህ ተረጋግጧል፡፡ የዳኝነት ገንዘብ ካልከፈልክ በቀር ፋይል አይከፈትም ለተባለው ከሣሽ ግን ይህ ዓይነቱ ትዕዛዝ የመጨረሻ ነው፡፡ ሌላ የሚጠበቅ የሥረ-ነገር ፍርድ የለውም፡፡ ስለሆነም የዳኝት ገንዘብ ለመክፈል አቅም ሳይኖረኝ ክርክሬና ማስረጃዬ በአግባቡ ሳይታይ አቅም እንዳለኝ ተቆጥሮ የዳኝነት ገንዘብ ክፈል መባሌ ተገቢ አይደለም የሚል ከሆነ የተሰጠው ትዕዛዝ የመጨረሻ እንደመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/1/ መሠረት የይግባኝ አቤትታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/3/ … ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የሚለውን አነጋገር ከላይ በተመለከተው መሠረት ከሁለት ማዕዘን አንፃር ሳይመለከት በደፈናው ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች ናቸው በሚለው ድንጋጌ ሠፍሮ የሚገኝ መሆኑን ብቻ በማየት አመልካች በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡



## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የዳኝነት ገንዘብ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ከስር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን መርምሮ ሊወስን ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18993 በጥር 30 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ